በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# ኦርቶዶክሳዊ ጋብቻ - ክፍል 6

## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon3@gmail.com

*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

**ግንቦት ፲፰ ቀን ፳፻፱ ዓ.ም.**

# የጋብቻ ሕይወታችን የሚመራበትን ሥርዓት ማዘጋጀት

- በዛሬው ትምህርታችን አዲስ የሚጀመር ቤተሰባዊ ሕይወት እንዴት ሥርዓት እንደሚበጅለት እንማራለን፡፡
- ማንኛውም ቤተሰብ የሚተዳደርበት ሥርዓት ያስፈልገዋል፡፡
- ያለ ሥርዓትና ያለ መመሪያ የሚሄድ ቤተሰብ አቅጣጫውንና ግቡን ይስታል፡፡
- ስለዚህ ለገንዘባችን፣ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን፣ ለማኅበራዊ ሕይወታችነ፣ ለትምህርት፣ ለልጆች… እንዴት ሥርዓት እንደምናበጅለት እንማራለን፡፡
- ‹‹ ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና፥ አንዳንዶች ይህን ሲመኙ፥ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ፡፡ አንተ ግን፥ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፥ ከዚህ ሽሽ፤ ጽድቅንና እግዚአብሔርን መምሰል እምነትንም ፍቅርንም መጽናትንም የዋህነትንም ተከታተል፡፡ በአሁኑ ዘመን ባለ ጠጎች የሆኑት የትዕቢትን ነገር እንዳያስቡ፥ ደስም እንዲለን ሁሉን አትርፎ በሚሰጠን በሕያው እግዚአብሔር እንጂ በሚያልፍ ባለ ጠግነት ተስፋ እንዳያደርጉ እዘዛቸው፡፡ እውነተኛውን ሕይወት ይይዙ ዘንድ፥ ለሚመጣው ዘመን ለራሳቸው መልካም መሠረት የሚሆንላቸውን መዝገብ እየሰበሰቡ፥ መልካምን እንዲያደርጉ በበጎም ሥራ ባለ ጠጎች እንዲሆኑ፥ ሊረዱና ሊያካፍሉም የተዘጋጁ እንዲሆኑ ምከራቸው፡፡››
  *ቀዳ ጢሞ 6፡10፣11፣17-19፡፡*
- ለገንዘብ የምንሰጠው ዋጋ ገንዘብን ከመውደድ ይለያል፡፡ ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነው፡፡
- ባለጠግነትም ራስን ብቻ የሚያስደስቱበት ሆኖ በዚህ ዓለም የሚያልፍ ባለጠግነት እንዳይሆን መጽሐፍ ያስጠነቅቀናል፡፡
- ቅዱስ እንጦንስ የገዳማዊ ሕይወት መሥራች አባት ነው፡፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዶ ‹‹ፍጹም ልትሆንስ ብትወድ ያለህን ሸጠህ ለድሆች ሰጥተህ ተከተለኝ…›› *ማቴ 19፡21፡፡* ያለውን የጌታችንን ቃል ሰማ፡፡ አባቱ ሲያርፍ የወረሰውን ለእህቱ የምትፈልገውን ሰጥቶ የተቀረውን ሁሉ ለድሆች ሰጥቶ ወደ አረፈው አባቱ አስከሬን ቀርቦ ‹‹ሁሉንም ያለፈቃድህ ትተህ ሄድህ፣ እኔ ግን በፈቃዴ ዓለምን እተወዋለሁ…›› ብሎ መነነ፡፡
- ወደዓለም የመጣነው ምንም ሳንይዝ ነው፡፡ ምንም ልንወስድም አይቻለንም፡፡ *ቀዳ ጢሞ 6፡7-8፡፡*

# የጋብቻ ሕይወታችን የሚመራበትን ሥርዓት ማዘጋጀት

- ‹‹ ብልና ዝገት በሚያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው በሚሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ፤ ነገር ግን ብልም ዝገትም በማያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው በማይሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ፤ መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናልና። የሰውነት መብራት ዓይን ናት። ዓይንህ እንግዲህ ጤናማ ብትሆን፥ ሰውነትህ ሁሉ ብሩህ ይሆናል፤ ዓይንህ ግን ታማሚ ብትሆን፥ ሰውነትህ ሁሉ የጨለመ ይሆናል። እንግዲህ በአንተ ያለው ብርሃን ጨለማ ከሆነ፥ ጨለማውስ እንዴት ይበረታ! ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም፤ ወይም አንዱን ይጠላል ሁለተኛውንም ይወዳል፤ ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል፤ ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም። ስለዚህ እላችኋለሁ፥ ስለ ነፍሳችሁ በምትበሉትና በምትጠጡት፥ ወይም ስለ ሰውነታችሁ በምትለብሱት አትጨነቁ፤ ነፍስ ከመብል ሰውነትም ከልብስ አይበልጥምን? ወደ ሰማይ ወፎች ተመልከቱ፤ አይዘሩም አያጭዱምም በጎተራም አይከቱም፥ የሰማዩ አባታችሁም ይመግባቸዋል፤ እናንተ ከእነርሱ እጅግ አትበልጡምን? ከእናንተ ተጨንቆ በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ መጨመር የሚችል ማን ነው? ስለ ልብስስ ስለ ምን ትጨነቃላችሁ? የሜዳ አበቦች እንዴት እንዲያድጉ ልብ አድርጋችሁ ተመልከቱ፤ አይደክሙም አይፈትሉምም፤ ነገር ግን እላችኋለሁ፥ ሰሎሞንስ እንኳ በክብሩ ሁሉ ከነዚህ እንደ አንዱ አልለበሰም። እግዚአብሔር ግን ዛሬ ያለውን ነገም ወደ እቶን የሚጣለውን የሜዳን ሣር እንዲህ የሚያለብሰው ከሆነ፥ እናንተ እምነት የጎደላችሁ፥ እናንተንማ ይልቁን እንዴት? እንግዲህ። ምን እንበላለን? ምንስ እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን? ብላችሁ አትጨነቁ፤ ይህንስ ሁሉ አሕዛብ ይፈልጋሉ፤ ይህ ሁሉ እንዲያስፈልጋችሁ የሰማዩ አባታችሁ ያውቃልና። ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል። ነገ ለራሱ ይጨነቃልና ለነገ አትጨነቁ፤ ለቀኑ ክፋቱ ይበቃዋል። ›› ማቴ 6፡19-34።
- ለቤተሰባዊ ሕይወታችን የምናዘጋጀው ሥርዓት የሚመነጨው ከላይ ከተጠቀሰው የጌታችን ትምህርት ነው።
- ለትዳራችን የሚሆነውን ሥርዓት የምንዘረጋው የእግዚአብሔርን ሕግና ሥርዓት በሚቃረን መልኩ መሆን የለበትም። ለዚህ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን።

# የጋብቻ ሕይወታችን የሚመራበትን ሥርዓት ማዘጋጀት

1. ገንዘባችንን የምናስተዳድርበት ሥርዓት
   1. *ገንዘብና ፍቺ፡-* ዛሬ በርካታ ትዳር ይፈርሳል፤ አንዱ ምክንያትም የገንዘብ ጉዳይ ነው፡፡ መጽሐፋችን ለነገ አትጨነቁ ሲል በጀት አይኑራችሁ ማለቱ አይደለም፡፡
   2. ገንዘብና *ቅዱሳት መጻሕፍት ፡-* (2/3ኛው የምሳሌ መጻሕፍት ስለ ገንዘብ ይናገራሉ)፡፡
      - ጌታችን በምሳሌ ካስተማራቸው ትምህርቶች 2/3ኛው ያህል ስለገንዘብና ስለበለጠግነት መሆኑ ስለምን ይመስለናል?
      - ገንዘብ ከእግዚአብሔር ለቤተሰቡ አካላት የተሰጠ ስጦታ ነው፡፡
      - ከባልም ይምጣ ከሚስት የሚገባው ወደ አንድ ቋት ነው፡፡
      - በብራችን ላይ ይህ ለባል ይህ ደግሞ ለሚስት ነው የሚል ተጽፎበት አናገኝም፡፡
      - በባንክ ደብተራችን ላይ የተጻፍነው እኛ ብንሆንም ገንዘቡ የተሰጠን ከእግዚአብሔር ነው፡፡
   3. ገንዘባችንን የምናስተዳድርባቸው ጠቃሚ ዘዴዎች (መንገዶች)
      I. ስለ ሀብት ዓለምና እግዚአብሔር የሚሉን ምንድር ነው? ዓለም የሌላውን ሰው ገንዘብ እንደልብህ ተጠቅሞ ባለጠጋ መሆንን (መኪና፣… መግዛት) ስትሰብክ በክርስትናው ደግሞ ባለጠግነት ልጅነታችን (ጥምቀት..) መሆኑንና ገንዘብም መጠቀሚያ ስጦታ እንደሆነ መረዳት፡፡
      II. ገንዘብ ጋብቻን ደስታንና ሐሴትን የተሞላ እንዲሆን እንደማያደርገው ማወቅ፡፡
      III. መንፈሳዊነትና የጋብቻ ሕይወት ገንዘብን የሚመለከቱበት መንገድ ተቀራራቢ መሆኑን መረዳት፡፡
      IV. እግዚአብሔር ለጋብቻ የመረጠው ተቃራኒውን ነው፡፡ እኛ ገንዘቡን ለግጭት … እንጠቀምበታለን፤ እርሱ ግን ባልና ሚስቱን ለማቀራረብ ለማግባባት እንደሚጠቀምበት ማወቅ፡፡
      V. ያለን ሁሉ የእግዚአብሔር ነው፡፡ ‹‹ወደ ዚህ ዓለም ስንመጣ ይዘን የመጣነው ምንም የለንምና ከዚህ ዓለም ስንወሰድም ይዘነው የምንሄደው የለም፡፡››

# የጋብቻ ሕይወታችን የሚመራበትን ሥርዓት ማዘጋጀት

1. ***ገንዘባችንን የምናስተዳድርበት ሥርዓት…***

   VI. እኛ የእግዚአብሔር ገንዘብ አስተዳዳሪዎች ወይም መጋቢዎች ነን፡፡ ገንዘቡንም የምናስተዳድረው እንደ እግዚአብሔር ዕቅድና ፈቃድ ነው፡፡

   - ‹‹ብልጥግናና ክብር በእኔ ዘንድ ነው፥ ብዙ ሀብትና ጽድቅም፡፡›› ***ምሳሌ 8፡18፡፡***
   - ‹‹ነገር ግን የዚህ ዓለም ገንዘብ ያለው፥ ወንድሙም የሚያስፈልገው ሲያጣ አይቶ ያልራራለት ማንም ቢሆን፥ የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ እንዴት ይኖራል?›› ብሎ የሚጠይቀን የሠተንን ገንዘቡን በአግባብ ለማስተዳደር አለመቻላችንን ሊገልጽልን ነው፡፡ ***ቀዳ ዮሐ 3፡17፡፡***

   VII. በትዳር ወጪውን የሚመዘግብ፣ አውጥቶ የሚከፍል፣ እንደ በጀቱ እየተጠቀምን መሆኑን የሚከታተል አንድ ሰው ያስፈልጋል፡፡ ብዙ ጊዜ ይኽን የሚሠሩት ሴቶች (ሚስቶች) ናቸው፡፡

   VIII. ገንዘቡ የእግዚአብሔር ነውና፡- በበጀቱ ውስጥ የሚያዙ ዝርዝር ነገሮች በባልና ሚስት መካከል ተገቢ ውይይትና ስምምነት ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

   IX. ከጋብቻ በፊት፡-

      I. ቢያንስ የእግዚአብሔርን ገንዘብ እንዴት እጅግ መልካም በሆነ መንገድ እንደምናስተዳድር መማር ይገባል፡፡

      II. ጋብቻችን የሚመራበትን ግባችንን፣ ዓላማችንን ደረጃ እናዘጋጅ፣ በየዓመቱ የተወሰኑ ቀናትን ወስደን እንገምግመው፡፡

- ‹‹አካሄዳችሁ ገንዘብን ያለ መውደድ ይሁን፥ ያላችሁም ይብቃችሁ፡፡›› ዕብ 13፡5፡፡
- ‹‹ገንዘብንም በመመኘት በተፈጠረ ነገር ይረቡባችኋል፤ ፍርዳቸውም ከጥንት ጀምሮ አይዘገይም ጥፋታቸውም አያንቀላፋም፡፡›› ***ካል ጴጥ 2፡3፡፡***

# የጋብቻ ሕይወታችን የሚመራበትን ሥርዓት ማዘጋጀት

1. ገንዘባችንን የምናስተዳድርበት ሥርዓት…

   X. እግዚአብሔር ገንዘብን

      I. ታማኝነታችንን ለመመዘን

      II. ፍቅሩን ለማሳየት

      III. ተጋቢዎቹን በመወያየት የበለጠ እንዲቀራረቡ ለማድረግ ይጠቀምበታል፡፡

   XI. ተጋቢዎች እርስ በርስ መግባባት ሲሳናቸው እያንዳንዳቸው ከሁሉ የተሸለውንና ከሁሉ የባሰውን ሁኔታና ተስማምተው ሊኖሩበት የሚችሉት በምን እንደሆነ ይጻፉ፡፡

   XII. አንድ ከፍ ያለ ነገር ነገር ለመግዛት ከፈለጋችሁ ሦስት የዋጋ ማቅረቢያዎችን ወስዳችሁ ለአንድ ወር አቆዩት፡፡ ምክንያቱም ሌላ አስቀድሞ የሚያስፈልገን ነገር ተፈጥሮ የቀደመውን ነገር ሳንገዛው እንችላለን፡፡

   XIII. በርካታ ሴቶች ወይም ሚስቶች ብዙ ገንዘብ አውጥተው መግዛት ሲፈልጉ የሚገዙት ልብስ ወይም ምግብ ሲሆን ወንዶች ደግሞ መኪና፣ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች፣ ኮምፒዩተሮች፣ ጀልባ ወይም አውሮፕላን ለየቅል መሆኑን ማወቅ፡፡

   XIV. ብድርና የብድር ካርድ፡-

   ***ይትበሃሎች፡-***

      I. ‹‹የግድ መበደር ይኖርብሃል፡፡›› ይህን አባባል የፈጠሩት አይሁድ ናቸው፡፡ እነርሱ ግን ይህን አይጠቀሙበትም፡፡ በዚህች ምድር የኖሩ አያቶቻችን ፈጽመው ገንዘብ አልተበደሩም፡፡ ይልቁኑ ቆጥበው ከቆጠቡት ገዙበት እንጂ፡፡

      II. ‹‹የብድር ካርዳችንን በዘዴ እንጠቀምበት፡፡›› እውነታው ያለሞኝነት መጠቀም ነው፡፡ ምክንያቱም ከኪሳችን ገንዘብ አውጥተን የምንገዛ ብንሆን እንጠነቀቃለን፡፡ የማንገዛውን ሁሉ ግን በብድር ካርዳችን እንገዛለን፡፡

      III. ‹‹ወለድ መክፈል ቀረጥን ለመክፈል አለመፈለግ ነው፡፡›› ይህን የሚል እውነታ የለም፡፡

# የጋብቻ ሕይወታችን የሚመራበትን ሥርዓት ማዘጋጀት

*በጀት*

*አገልግሎቱ ወይም ጥቅሙ፡-*

- ተጋቢዎቹን ማቀራረብ
- እግዚአብሔርን ለመታመንና ትእዛዙንም ለማክበር
- ባወጣነው በጀት አጥር ዙሪያ ነጻነት ተሰምቶን በነጻነት እንድንንቀሳቀስ ነው፡፡

- ስለ በጀታችሁ አብራችሁ ጸልዩ፣ በጀቱንም አብራችሁ አዘጋጁት፡፡
- ከጋብቻ በፊት የአንድ ዓመት በጀታችንንና እቅዳችንን መሥራት ይኖርብናል፡፡
- ከዕዳ የምንወጣበት የተሻለው መንገድ ተቃራኒውን ማከናወን ነው፡፡ ይህም ወደ ዕዳ ለመግባት ያደረግነውን ተቃራኒ ነገር መልሰን ብንፈጽም ከዕዳ ራሳችንን መገደብ እንችላለን፡፡
- ገንዘባችንንም ሆነ ራሳችንን ለእግዚአብሔር እንስጥ፡፡ በመቀጠልም ላወጣነው ዕቅድ ተገዢ እንሁን፡፡ ዕቅዳችንን ከመተውም ሆነ ከመለወጥ እንቆጠብ፡፡
- የሰማይ ወፎች ያለማቋረጥ ምግባቸውን ለማግኘት ወዲያና ወዲህ ይላሉ ይሠራሉ፡፡ ይሠራሉ እንጂ አይጨነቁም፡፡
- ሰውም እየሠራ በገደቡ ሳይጨነቅ መኖር ይጠበቅበታል፡፡
- ‹‹እጅግ ወይም ጥቂት ቢበላ የሠራተኛ እንቅልፍ ጣፋጭ ነው የባለጠጋ ጥጋብ ግን እንቅልፍን ይከለክለዋል፡፡›› *መክብብ 5፡12፡፡*
- ‹‹እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ ባለጠግነትንና ሀብትን መስጠቱ፥ ከእርስዋም ይበላና እድል ፈንታውን ይወስድ ዘንድ በድካሙም ደስ ይለው ዘንድ ማሠልጠኑ ይህ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፡፡» *መክብብ 5፡19፡፡*
- ‹‹እኔም እላችኊለሁ፥ የዓመፃ ገንዘብ ሲያልቅ በዘላለም ቤቶች እንዲቀበሉአችሁ፥ በእርሱ ወዳጆችን ለራሳችሁ አድርጉ፡፡ » *ሉቃ 16፡9፡፡*

# የጋብቻ ሕይወታችን የሚመራበትን ሥርዓት ማዘጋጀት

***በየወሩ በጀታችንን የምናስቀምጥባቸው አሥራ ሁለቱ  መሳቢያዎች ወይም ፖስታዎች***

1. አሥራት
2. ግብር ወይም ቀረጥ

   እኛ የምንጠቀምበት ገንዘብ የወሩ ጠቅላላ ገቢያችን አሥራትና ግብር ከተቀነሱለት በኋላ ያላው ገንዘብ ነው፡፡
3. 30% ለቤት ዕዳችን፡- ለኢንሹራንስ፣ ግብር፣ ለመብራት ውሃ ለመሳሰሉትና ለጥገና
4. 15% ለመኪናችን ወይም ለመጓጓዣ፡- ለምዝገባዎች፣ ለነዳጅ፣ ለጥገና ወዘተ
5. 16% ለምግባችን
6. 5% ለቤተሰቡ አባላት ለሚሆን ልብስ
7. 5% ለኢንሹራንስ (ለሕይወት፣ ለጤና፣ ...)
8. 5% ለጤናችን ወጪ (ጥርስ፣ ሆስፒታል፣ መድኃኒቶች፣ ኮስሞቲክ ሰርጀሪ...)
9. 7% ለመዝናኛ (ከከተማ ወጥቶ ለመዝናናት፣ ዓለምን ለመጎብኘት... ከቤት ውጪ ለመመገብ...)
10. 7% ለሌሎች ጥቃቅን ወጪዎች (ሽቶ፣ ሻምፖ፣ ስጦታ ...)
11. 5% ለቁጠባ
12. 5% ዕዳን ለመክፈል፡፡

- እርስ በርስ መግባባት ባይኖር ተስማምተን ወዳስቀመጥነው ተመልሰን ማስተካከልና ያላስቀመጥነውንና ያልተግባባንበትን ለይተን በማውጣት መተው ወይም መልሰን በመመካከር ማካተት ይገባናል፡፡

# የጋብቻ ሕይወታችን የሚመራበትን ሥርዓት ማዘጋጀት

2. ***መንፈሳዊ ሥርዓቶች***
    1. በየትኛይቱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የጋብቻ ሥርዓታችን ይፈጸማል… በየትኛው አጥቢያ እናስቀድሳለን፣ ጉባኤ እንሳተፋለን፣ ልጆቻችን በየት እየተማሩ ያድጋሉ፣ የልጆቻችን የማይለወጡ ጓደኞቻቸው እነማን ናቸው?
    2. የንስሐ አባት፡- ባልም ሚስትም ሁለት አባት ሊኖራቸው ኤአችልም አንድ አባት እንጂ… በቤ/ክ ለምን ያህል ሰዓት አገልግሎት እንሰጣለን… በቤታችን የምናደርገው ጸሎት… የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት…
    3. ለጋብቻው የሚያስፈልግ መንፈሳዊ ምክር ከማን እንዴት እንቀበላለን? እነዚህ ሁሉ ሥርዓት ያስፈልጋቸዋል፡፡
    4. መንፈሳዊ መርሐ ግብሮቻችንም ሥርዓት ሊኖራቸው ያስፈልጋል፡፡
3. ***የማኅበራዊ ሕይወት ሥርዓቶች***
    1. ከአማቾቻችን ጋር የሚኖረን ግኑኝነት
    2. ዘመዶቻችንና ጓደኞቻችን
    3. የዕረፍት ጊዜያችን
    4. ከቤት ውጪ አብሮ መብላትና ቅዳሜና እሁድን አጠቃቀም ከበጀታችን ሳንወጣ ሥርዓት ያስፈልገዋል፡፡
4. ***ትምህርት፣ የተሻለ ዕድገት እና ሥራ***… ለማከናወን የተስማማንበት ሥርዓት ያስፈልጋል፡፡ ባል ሲማር ሚስት ነፍሰ ጡር ሆና ሥራም መሥራት ቢሳናትስ፣ ድንገት ከሥራ መሰናበት ቢኖርስ?… ተመካክረን ሥርዓት እናብጅለት፡፡
5. ***ልጆች***
    1. መቼ ልጆች እንዲኖረን እንሻለን? ሰቲቱ 32 ዓመት ሳይሆናት ባል ፒ ኤች ዲዬን ስጨርስ ቢልስ? ሥርዓት…
    2. ምን ያህል? 2፣ 4፣ 6፣ 8፣ …? ተነጋገሩ ሥርዓት አድርጉለት፡፡
    3. እንዴት እናሳድጋቸው? ልጆችን እግዚአብሔርን እንዲፈሩ አድርገን ለማሳደግ የሚያስፈልገን ችሎታ ምንድን ነው? አስቀድማችሁ ተነጋገሩ ሥርዓት አድርጉለት፡፡

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons surf :

www.zeorthodox.org

… ክፍል ሰባት ይቀጥላል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።